# የእምቧይ ካብ

ተከፍሎት እንዲያስብ
በስኮላርሺፕ መጥቶ
ያ አራዳ ዶክተር
ተራራ ላይ ወጥቶ
ይኸው አልተመለሰም
ምን ይሻላል ከቶ?
ወራቶች ከነፉ
አስቦ አልጨረሰም
ግራ የገባው ነገር
ለወሬ አይመችም
ሴትዮዋን ጥሩዋት
ያቺ አሻንጉሊቱን
እርሷ ታውቅ እንደሆን
ይህንን ጸባዩን
ተከታዩ አፍሩዋል
የለውም ወዳጅ
ተራራው ላይ ይቅር
ለማንም አይበጅ።
ሴትዮዋም የለች
መቀሌ ነጉዳለች
ጉሮ ወሸባ ጊዜ
ዘመድ ሰላፈራች
ይቅርታ ያለችው
ሚኒሶታ ሳለች
አዲስ አባ ጠፍቶ
ተለጣፊ መስራች።
ጄኔራል አንዳርጌም
ሥራ ብዙ ሆኗል
ሰላም በቃኝ ብሎ
ጠሩን አንቀሳቅሷል
የፓልቶክ ብርጌዱን
አስመራ ጠርቶታል።
ብሬ እና ሞገስም
የገቡበት ጠፍቷል
በሬ ወለደ ሁሉ
በየፊናው ሄዷል
አንድ የቀናው የለም
ሁሉም ኩሽም ብሏል
ሽማግሌው ቀሎ
ቁልቁለቱን ሄዷል
ያፈንጋጩ ቡድን
በጣም ተደናግጧል
የውስጡም የውጭው
የሚይዘው አጥቷል።
ምድረ ሆዳም ባንዳ
ለሆዱ ያደረ
የሕዝብ ትግል ከድቶ
ከጠላት ያበረ
አናውቅህም ብሎ
ሕዝብ እያሳፈረ
ላያዛልቅ ነገር
ከጠላት ተዛምዶ
መፈራረስ ይዟል
የእምቧይ ካብ ተንዶ።

መጋቢት 2000 ዓ.ም
አዳነች መኮ
ቫንኮቨር፣ ካናዳ